## በ FERPA ሥር መብትን ማሳወቅ

የ ቤተሰብ ትምህርታዊ መብቶችና የግል ጉዳይ የመከበር ድንጋጌ (The Family Educational Rights and Privacy Act (FERPA)) ለወላጆችና እድሜአቸው 18 ዓመት እና ከዚያም በላይ የሆኑ ተማሪዎች (“ብቁ የሆኑ ተማሪዎች”)፤ የተማሪዎችን የትምህርት መረጃዎች በሚመለከት ረገድ የተወሰኑ መብቶችን ያጎናጽፋል። እነዚህም መብቶች፤

**(1)** ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች፣ (DCPS) መረጃዎችን እንዲሰጥ ጥያቄዎች በቀረቡለት በ 45 ቀናት ውስጥ የተማሪውን የትምህርት **መረጃ ዎች የመመርመር እና የማጣራት መብት።** ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ለመመርመር የሚፈልጉትን መረጃ(ዎች) በመጥቀስ ለትምህርት ቤቱ ርእሠ መምህር ጥያቄዎቹን በጽሑፍ ማቅረብ አለባቸው። የትምህርት ቤቱ ርእሠ መምህርም ሆነ ወይም አግባብ ያለው የትምህርት ቤት ባለሥልጣን መረጃው የሚገኝበትን ሁኔታዎች በማመቻቸት፣ መረጃዎቹ ሊመራመሩና ሊታዩ የሚችሉበትን ጊዜና ቦታ በመጥቀስ ለወላጆችም ሆነ ወይም ብቁ ሆነው ለሚገኙ ተማሪዎች ያስታውቃል።

**(2)** ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ በ FERPA የተማሪው ግላዊ መብቶችሥር፣ የተማሪው የትምህርት መረጃዎች፣ ትክክል አይደለም፣ ያሳስታል፣ ተዛብቷል፣ እውነቱን ያዛንፋል ብለው የሚያምኑበትን፣ **እንዲቃና፣እንዲስተካከል የመጠየቅ መብት።** ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ ትክክል አይደ ለም፣ተዛብቷል፣ ተሳስቷል ብለው የሚያምኑበትን የተማሪውን የትምህርት መረጃዎች ተስተካክሎ እንዲቀርብ ዲሲፒኤስን መጠየቅ የሚችሉ ሲሆን፣ ከተሳሳተው መረጃ ውስጥ የትኛው ክፍል እንዲስተካከል እና እንዲቃና እንደሚፈልጉ፣ እንዲሁም ለምን ትክክል ሊሆን እንዳልቻለ እና ለምንስ መለወጥ እንደሚያስፈልገው ጭምር በግልጽ በመጥቀስ ለትምህርት ቤታቸው ርእሠ መምህር ችግሩን ማቅረብና ማመልከት ይችላሉ። በጥያቄውም መሠረት፣ ዲሲፒኤስ የተሳሳተውን መረጃ ለማስተካከል የማይፈልግ ሆኖ ከተገኘ፣ ትምህርት ቤቱ፣ ስለ ደረሰበት ውሳኔ ለወላጅ ወይም ብቁ ሆኖ ለሚገኘው ተማሪ በማስታወቅ መረጃውን ለማቃናት ለሚያ ስችል አቤቱታ ሰሚ አካል ማቅረብ እንደሚችሉ ማሳወቅ አለበት። ወላጅ ወይም ብቁ ሆኖ የሚገኝ ተማሪ፣ ጉዳያቸው በችሎት እንዲታይላቸው መብት ያላቸው መሆኑ በሚገለጽላቸው ሰዓት፣ ስለ ችሎቱ ሂደት ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጣቸው ይደረጋል።

**(3)** ያለ ማንም ስምምነት FERPA የተማሪው መረጃዎች ይፋ እንዲወጡ ከሚያዝበት ደረጃ በስተቀር፣ በተማሪው የትምህርት ማኅደር ውስጥ የሚገኙ **ግላዊነትን የሚያመለክቱ መለያ መረጃዎች ሁሉ ይፋ እንዲወጡ የመስማማት መብት።** ዲሲፒኤስ፣ ሕጋዊ የሆነ ትምህርት ነክ ፍላጎት ይኖራቸዋል ብሎ ለተቀበላቸው ለትም ህርት ቤት ባላ ሥልጣናት፣ ያለ ፈቃድ ስምምነት ይፋ እንዲሆንላቸው FERPA ያዛል። የትምህርት ቤት ባለ ሥልጣን፣ በዲሲፒኤስ፣ የተቀጠረ አስተዳዳሪ፣ ሱፐር ቫይዘር፣ መምህር ወይም ድጋፍ ሰጪ የትምህርት ቤት አባል (የጤና ወይም የሕክምና ቡድን አባል እና የሕግ አስከባሪዎች ቡድን አባላትን ጨምሮ)፣ ልዩ ተግባራትን (ለምሳሌ ያህል እንደ ጠበቃ፣ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ የሕክምና አማካሪ ወይም ፈውስ ሰጪ (therapist)) የመሳሰሉትን እንዲያከናውኑ ዲሲፒኤስ የተኮናተራቸው፤ ወይም ኦፊሽያል በሆኑ እንደ የሥነ ሥርዓት ወይም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፣ ወይም የተሰጠውን ወይም የተሰጣትን ተግባር እንዲያካሂድ እንድታካሂድ ሌላ የትምህርት ቤት ባለሥልጣን መርዳትን ያካትታል። የትምህርት ቤት ባለሥልጣን፣ ሙያዊ የኃላፊነት ተግባሩን ለመወጣት እንዲችል ወይም እንድትችል የትምህርት ማስረጃዎችን መመርመር ከፈለገ ወይም ከፈለገች ሕጋዊ ትምህርታዊ ዝንባሌ ይኖረዋል ወይም ይኖራታል ማለት ነው።

**(4)** ***የመረጃዎችን ጥንቅር ይፋ እንዳይወጣ የማገድ መብት።*** ደንቡ በሚፈቅደው፣ ባለው መብት እና በራሱ ሥልጣን በመጠቀም፣ ዲሲፒኤስ ያለ ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች ስምምነት፣ አብዛኛውን ጊዜ ጉዳት የማያስከትሉ ወይም ችግር የማያደርሱ ወይም የግል መብትን የማይጻረሩ ተብለው የሚገመቱ መሠረታዊ “የመረጃዎች ጥንቅር” በዲስትሪክቱ ሕግ ጥላ ሥር እና በ FERPA አማካይነት፣ ያለ ወላጆች ስምምነት ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች ፍቃድ መረጃዎችን ይፋ ማድረግ ይችላል። የመረጃዎችን ጥንቅሩም የሚከተሉትን ያካትታል።

- ሀ. የተማሪው ስም
- ለ. የተማሪው አድራሻ
- ሐ. የተማሪው የተመዘገበ የስልክ ቁጥር
- መ. የሚማርበት ትምህርት ቤት ስም
- ሰ. በኦፊሲየል ዕውቅ በሆኑ ክንዋኔዎችና ስፖርቶች መሳተፍ
- ረ. የአትሌቲክ ቡድኖች አባላት ክብደትና ቁመት
- ሠ. ዲፕሎማዎች እና ሽልማቶች
- ሽ. ተማሪው የተወለደበት ዘመንና የትውልድ ቦታ
- ቀ. ቀድሞ የተማረበት ትምህርት ቤት ስም
- በ. ትምህርት ገበታ ላይ የተገኘባቸው ቀናት

***ወላጆች ወይም ብቁ ሆነው የሚገኙ ተማሪዎች፣ በተማሪዎች የትምህርት ቤት ምዝገባ ወቅት ሊገኝ የሚችለውን የ*** “Release of Student Directory Information Form” (“***የተማሪ መረጃዎችን ይፋ የማድረጊያ ቅጽ***”) ***አጠናቆ በመሙላት ከዓመቱ የትምህርት ዘመን የመጀመሪያው ዕለት ሁለት ሣምንታት ባለ ጊዜ ውስጥ ከላይ የተመለከቱትን መረጃዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ ይፋ እንዳይወጣ በመግለጽ፣ በጽሑፍ*** 1200 First St NE, 12th Floor Washington, DC 20002 ***ላይ ለሚገኘው ለ*** Data and Accountability ***ጽሕፈት ቤት በማቅረብ ዲሲፒኤስን ማስገንዘብ ይችላሉ። ዲሲፒኤስ፣ የመረጃውን ጥንቅር ይፋ ከማውጣቱ በፊት ቀደም ብሎ የእርስዎን የጽሑፍ ስምምነት እንዲያገኝ ከፈለጉ፣ ይህንን ቅጽ ብቻ አጠናቀው መሙላት እንዳለብዎት እባክዎን ልብ ይበሉ።***

(5) ***ዲሲፒኤስ*** FERPA ***ተሟልተው እንዲገኙ የሚጠብቃቸውን ጉዳዬች ለማሟላት ያለመቻልን በሚመለከት፣ ለዩኤስ የትምህርት መምሪያ አቤቱታ የማቅረብ መብት።*** FERPA ን ሕገ ደንብ የሚመራው ***ድርጅት ጽሕፈት ቤት ስምና አድራሻ ቀጥሎ የተመለከተው ነው።***

Family Policy Compliance Office
U.S. Department of Education
400 Maryland Avenue, SW
Washington, DC 20202-5901